# እንኳን ደስ አለን ለሁላችን!!

*ይገርማቹሀል ይሄንንና እዚህ ላይ አሁን ለእናንተ ያላቀርብኩትን በግእዝ (አማርኛ) ፊደል ቁጥርና የቁጥር ስሞች መቸ፣ የት፣ እንዴት፣ ተፈጠሩ ? የሚለውንና ባጠቃላይ በቋንቋችን ላሉ ሌሎች ምላሽ ያልነበራቸው ጉዳዮችን ምላሽ የሚሰጥ የጥናትና ምርምር ሥራ ከሐሳብ ወደ ተግባራዊ ሥራ ተሸጋግሬ መሥራት የጀመርኩት ዐሥራዎቹ መገባደጃ የዕድሜ ክልል እያለሁ ጀምሬ ነበር። ከብዙ ዓመታት ድካምና ጥረት በኋላም ሥራውን ጨረስኩ ባልኩ ጊዜ ምቹ ሁኔታና ጊዜ ይመጣል ብየ ብጠብቅ ብጠብቅ ቀጠሮ ያልያሳዘኝ ነገር መቅረቱ አሳሰበኝና ከሁለት ዓመታት ወዲህ ጀምሬ ለአንዳንድ የመገናኛ ብዙኃንና ዕውቅና ለሚሰጡ የሚመለከታቸው መንግሥታዊ ተቋማት አቀረብኩት። ታዲያ እዚያ ያሉት ሰዎች ፊደላት ካልተነቀነሱ ሞተን እንገኛለን የሚሉና ከዚያም አልፈው ወደ 91 የሚደርሱ ሆሄያትን አስወግደው በተቋም ስም መጽሐፍ እስከማሳተም የደረሱ ነበሩና በፊደላት ይቀነሱ አይቀነሱም ክርክር ዙሪያ አይቀነሱም የራሳቸው ጥቅምና አገልግሎት አላቸው ብየ ጥቅም አገልግሎታቸውን፣ ቢቀነሱ ቢወገዱ በቋንቋዎቻችን ላይ የሚያጋጥመውን ያላዩትን ያላስተዋሉትን ቋሚ ጉዳትና አደጋ እየዘረዘርኩ አጥጋቢ መልስ በመስጠቴ ዶክተሮቹ እነሱ የሀገርን ቅርስ ሀብትና እሴት ያህል ነገር ሲያዋርዱ ሲያንቋሽሹ ሳይገባቸውና ሳይረዱም በማንአለብኝነት ሲያስወግዷቸው ቅንጣት ያልተሰማቸው መልስ ሲሰጣቸው ክብራቸው እንደተደፈረ ጥቅማቸው እንደተነካ ቆጥረውት የጥናትና ምርምሩን ሥራ በተመለከተ በነበረን ውይይት* (session) *ላይ በግልጽ በአንደበታቸው በየመጽሔቱ በየጋዜጣው ሰድበኸናል ከአንድ የጥናትና የምርምር ወረቀት የማይጠበቅ በስድብና በዘለፋ የተሞላ ነው በማለት አቂመው ዕውቅናውንና ሌሎች ከእነሱ የሚጠበቁ ድጋፎችን ነፈጉኝ። አይገርምም ? አያሳዝንም? አያሳፍርም? ከዚያ በኋላም ለቃለመጠይቅ* (interview) *በቀረብኩባቸው የብዙኃን መገናኛ ዝግጅቶች ፊት ለፊት ተገናኝተን እንድንከራከር የቀጥታ ግብዣ ጥሪ ባቀርብም ሞኝህን ፈልግ ብለው ወይ ፍንክች ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ።*

*ከሥራየ ከፊሉን እነሆ ጋብዣቹሀለሁ ወደፊት እግዚአብሔር ከፈቀደና ለራሱም ለሀገሩም ታሪክ መሥራት ቋሚ ቅርስ ማቆየት የሚፈልግ ማንንና ምንን ዓይነት ጉዳይ መደገፍ እንዳለበት ያወቀ አስተዋይ ስፖንሰር(ድጋፍ ሰጭ) ካገኘሁ ሙሉውን ባለ* 500 *ገጽ የሥራውን መጽሐፍ ታገኙታላቹሀ።*






**ከረጅም ጊዜ ጀምሮ በሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ምኞች ዘንድ እዲሆን ሲፈለግ የነበረው ፍላጎት እውን ሆነ። በመሆኑም፦ በሀገራችን ባሕላዊ ቅርስ ላይ ገናናና ዓይነተኛ ዋጋ የሚጨምሩ ውስንነትን የሚቀርፉ የፈጠራ ሥራዎች፦**

1ኛ. **ከ26 የማይበልጡ የነበሩ የቁጥሮቻችንን ሥያሜዎች እስከ እልፍ ድረስ አባቶቻችን ያስቀመጡትን ሥያሜ የሚቀየርበት ርቀት በመጠበቅ ወጥ ካልሆነው ከምዕራባዊያኑ በተለየ መልኩ በየዐሥሮሹ ሥያሜ እየቀየረ በመቀጠል እስከ 48828 ዓይነት የቁጥሮች ሥያሜዎች እና 48828 ባዶ ወይም ምንም (ዜሮ) ያለው ትልቁ ስም ያለው ቁጥር ማለትም ኍልቆፍልፊታት ድረስ በማሳደግ ሲያስፈልግም ከዚያም በበለጠ ብዙ ጊዜ እጥፍ ሊሰፉ በሚችልበት አቋም ላይ ሆኖ በሥያሜዎች ብዛት በዓለም ከቶውንም ተወዳዳሪ የሌላቸው እና የማይደረስባቸው የቁጥሮች ሥያሜዎች ብዛትና ይሄን ያህል ባዶ ወይም ዜሮ ያለው ቁጥር ባለቤት በመሆን ብቸኛ ለመሆን ችለናል።**






## መሠረታተ አስማት ዘአኃዛት

## የአኀዞች መሠረታዊያን ስሞች

| ተ.ቁ | የቁጥሩ ስም በግዕዝ (አማርኛ) | በላቲን | ግዕዝ (አማርኛ) በ ፲ ሲጻፍ | የሚይዘው ባዶ (ዜሮ) ብዛት በ$10^x$ ሲቀመጥ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | እልፍ | əlf | $፲^{፬}$ | $10^4$ |
| 2 | አእላፍ | ɑ'lɑf | $፲^{፭}$ | $10^5$ |
| 3 | አእላፋት | ɑ'lɑfɑt | $፲^{፮}$ | $10^6$ |
| 4 | እልፊት | əlffit | $፲^{፯}$ | $10^7$ |
| 5 | እልፊታት | əlffitɑt | $፲^{፰}$ | $10^8$ |
| 6 | ብልፍ | bəlf | $፲^{፱}$ | $10^9$ |
| 7 | ባእላፍ | bɑ'əlɑf | $፲^{፲}$ | $10^{10}$ |
| 8 | ባእላፋት | bɑ'əlɑfɑt | $፲^{፲፩}$ | $10^{11}$ |
| 9 | ብልፊት | bəlffit | $፲^{፲፪}$ | $10^{12}$ |
| 10 | ብልፊታት | bəlffitɑt | $፲^{፲፫}$ | $10^{13}$ |
| 11 | ግልፍ | gəlf | $፲^{፲፬}$ | $10^{14}$ |
| 12 | ጋእላፍ | gɑ'əlɑf | $፲^{፲፭}$ | $10^{15}$ |
| 13 | ጋእላፋት | gɑ'əlɑfɑt | $፲^{፲፮}$ | $10^{16}$ |
| 14 | ግልፊት | gəlffit | $፲^{፲፯}$ | $10^{17}$ |
| 15 | ግልፊታት | gəlffitɑt | $፲^{፲፰}$ | $10^{18}$ |
| 16 | ድልፍ | dəlf | $፲^{፲፱}$ | $10^{19}$ |
| 17 | ዳእላፍ | dɑ'əlɑf | $፲^{፳}$ | $10^{20}$ |
| 18 | ዳእላፋት | dɑ'əlɑfɑt | $፲^{፳፩}$ | $10^{21}$ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 19 | ድልፊት | dəlffit |  | $10^{22}$ |
| 20 | ድልፊታት | dəlffitɑt |  | $10^{23}$ |
| 21 | ህልፍ | həlf |  | $10^{24}$ |
| 22 | ሃእላፍ | hɑ’əlɑf |  | $10^{25}$ |
| 23 | ሃእላፋት | hɑ’əlɑfɑt |  | $10^{26}$ |
| 24 | ህልፊት | həlffit |  | $10^{27}$ |
| 25 | ህልፊታት | həlffitɑt |  | $10^{28}$ |
| 26 | ውልፍ | wəlf |  | $10^{29}$ |
| 27 | ዋእላፍ | wɑ’əlɑf |  | $10^{30}$ |
| 28 | ዋእላፋት | wɑ’əlɑfɑt |  | $10^{31}$ |
| 29 | ውልፊት | wəlffit |  | $10^{32}$ |
| 30 | ውልፊታት | wəlffitɑt |  | $10^{33}$ |
| 31 | ዝልፍ | zəlf |  | $10^{34}$ |
| 32 | ዛእላፍ | zɑ’əlɑf |  | $10^{35}$ |
| 33 | ዛእላፋት | zɑ’əlɑfɑt |  | $10^{36}$ |
| 34 | ዝልፊት | zəlffit |  | $10^{37}$ |
| 35 | ዝልፊታት | zəlffitɑt |  | $10^{38}$ |
| 36 | ጥልፍ | ṭəlf |  | $10^{39}$ |
| 37 | ጣእላፍ | ṭɑ’əlɑf |  | $10^{40}$ |
| 38 | ጣእላፋት | ṭɑ’əlɑfɑt |  | $10^{41}$ |
| 39 | ጥልፊት | ṭəlffit |  | $10^{42}$ |


| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 40 | ጥልፊታት | ṭəlffitɑt |  | $10^{43}$ |
| 41 | ይልፍ | yəlf |  | $10^{44}$ |
| 42 | ያእላፍ | yɑ’əlɑf |  | $10^{45}$ |
| 43 | ያእላፋት | yɑ’əlɑfɑt |  | $10^{46}$ |
| 44 | ይልፊት | yəlffit |  | $10^{47}$ |
| 45 | ይልፊታት | yəlffitɑt |  | $10^{48}$ |
| 46 | ክልፍ | kəlf |  | $10^{49}$ |
| 47 | ካእላፍ | kɑ’əlɑf |  | $10^{50}$ |
| 48 | ካእላፋት | kɑ’əlɑfɑt |  | $10^{51}$ |
| 49 | ክልፊት | kəlffit |  | $10^{52}$ |
| 50 | ክልፊታት | kəlffitɑt |  | $10^{53}$ |
| 51 | ልልፍ | ləlf |  | 1054 |
| 52 | ላእላፍ | lɑ,əlɑf |  | 1055 |
| 53 | ላእላፋት | lɑ,əlɑfɑt |  | 1056 |
| 54 | ልልፊት | ləlffit |  | 1057 |
| 55 | ልልፊታት | ləlffitɑt |  | 1058 |
| 56 | ምልፍ | məlf |  | 1059 |
| 57 | ማእላፍ | mɑ,əlɑf |  | 1060 |
| 58 | ማእላፋት | mɑ,əlɑfɑt |  | 1061 |
| 59 | ምልፊት | məlffit |  | 1062 |
| 60 | ምልፊታት | məlffitɑt |  | 1063 |
| 61 | ንልፍ | nəlf |  | 1064 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 62 | ናእላፍ | nα,əlαf |  | 1065 |
| 63 | ናእላፋት | nα,əlαfαt |  | 1066 |
| 64 | ንልፊት | nəlffit |  | 1067 |
| 65 | ንልፊታት | nəlffitαt |  | 1068 |
| 66 | ሥልፍ | səlf |  | 1069 |
| 67 | ሣእላፍ | sα,əlαf |  | 1070 |
| 68 | ሣእላፋት | sα,əlαfαt |  | 1071 |
| 69 | ሥልፊት | səlffit |  | 1072 |
| 70 | ሥልፊታት | səlffitαt |  | 1073 |
| 71 | ፍልፍ | fəlf |  | 1074 |
| 72 | ፋእላፍ | fα,əlαf |  | 1075 |
| 73 | ፋእላፋት | fα,əlαfαt |  | 1076 |
| 74 | ፍልፊት | fəlffit |  | 1077 |
| 75 | ፍልፊታት | fəlffitαt |  | 1078 |


| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 76 | ጽልፍ | ṣəlf | | $10^{79}$ |
| 77 | ጻእላፍ | ṣɑʾəlɑf | | $10^{80}$ |
| 78 | ጻእላፋት | ṣɑʾəlɑfɑt | | $10^{81}$ |
| 79 | ጽልፊት | ṣəlffit | | $10^{82}$ |
| 80 | ጽልፊታት | ṣəlffitɑt | | $10^{83}$ |
| 81 | ቅልፍ | qəlf | | $10^{84}$ |
| 82 | ቃእላፍ | qɑʾəlɑf | | $10^{85}$ |
| 83 | ቃእላፋት | qɑʾəlɑfɑt | | $10^{86}$ |
| 84 | ቅልፊት | qəlffit | | $10^{87}$ |
| 85 | ቅልፊታት | qəlffitɑt | | $10^{88}$ |
| 86 | ርልፍ | rəlf | | $10^{89}$ |
| 87 | ራእላፍ | rɑʾəlɑf | | $10^{90}$ |
| 88 | ራእላፋት | rɑʾəlɑfɑt | | $10^{91}$ |
| 89 | ርልፊት | rəlffit | | $10^{92}$ |
| 90 | ርልፊታት | rəlffitɑt | | $10^{93}$ |
| 91 | ትልፍ | təlf | | $10^{94}$ |
| 92 | ታእላፍ | tɑʾəlɑf | | $10^{95}$ |
| 93 | ታእላፋት | tɑʾəlɑfɑt | | $10^{96}$ |
| 94 | ትልፊት | təlffit | | $10^{97}$ |
| 95 | ትልፊታት | təlffitɑt | | $10^{98}$ |
| 96 | ጵልፍ | P̣əlf | | $10^{99}$ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 97 | ጳእላፍ | Ṗαʼəlαf | | $10^{100}$ |
| 98 | ጳእላፋት | Ṗαʼəlαfαt | | $10^{101}$ |
| 99 | ጵልፊት | Ṗəlffit | | $10^{102}$ |
| 100 | ጵልፊታት | Ṗəlffitαt | | $10^{103}$ |
| 101 | ፕልፍ | pəlf | | $10^{104}$ |
| 102 | ፓእላፍ | pαʼəlαf | | $10^{105}$ |
| 103 | ፓእላፋት | pαˈəlαfαt | | $10^{106}$ |
| 104 | ፕልፊት | pəlffit | | $10^{107}$ |
| 105 | ፕልፊታት | pəlffitαt | | $10^{108}$ |

2ኛ. ለሀገራችን ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለም ሁሉ ያለእንከን ማገልገል የሚችል ዓለም እየተጠቀመበት ያለው በስሕተት የዓረብ ቁጥሮች በመባል የሚታወቁትን ቁጥሮች ያሉባቸውን ችግሮች ማለትም በአገልግሎት ላይ 0ን ወደ 6 8 እና 9፣ 1ን ወደ 4 እና 7፣ 3ን ወደ 8 በቀላሉ መለወጥ መቻሉ ለማጭበርበር የተመቸ ሆኖ መላው ዓለም ሲቸገር የኖረና እየተቸገረም ያለ በመሆኑ ከዚህ ችግር ፈጽሞ የፀዳና ፈጽሞ ለመጭበርበር የማይችሉ አዳዲስና ፍጹም ኢትዮጵያዊ የሆኑ አኃዞች ወይም ቁጥሮች መፈልሰፋቸው እውን ሆነ።




ተለዋጭ ቁጥሮች



3ኛ. አዳዲስ ፊደላት ለመፍጠር ያስፈለጉበት ምክንያቶች ሁለት ናቸው፡፡ አንደኛው ከሁለት ዐሥርተ ዓመታት በፊት በሀገራችን የተደረገውን የመንግሥት ለውጥ ተከትሎ የኦሮምኛ፣የአፋርኛ፣ሱማልኛ፣ጌድኦንና የመሳሰሉት ቋንቋዎች ተናጋሪዎች ቀድሞ ሲጠቀሙበት የነበረውን የአማርኛ ፊደላት በመተው ወደላቲኑ ሔዱ በላቲን ፊደላትም መገልገል ቀጠሉ እነሱም እንደሚሉት ለዚህ ውሳኔ የዳረጋቸው ምክንያት የአማርኛው የፊደል ገበታ አንዳንድ ድምፆቻችንን የሚወክሉ ፊደሎች ስለሌሉና በአማርኛ ቋንቋ ያሉ የአናባቢ ድምፆች በቂ ባለመሆናቸው  በማለት ነው፡፡ በአማርኛው የፊደል ገበታ ፊደሎቹ ባይኖሩም ልክ እንደ ትግርኛው በአማርኛው ወይም በግዕዙ ውስጥ የሌሉ ፊደላትን ለራሱ ቀርጾ እንደሚጠቀመው ሁሉ እነርሱም ይህንን መንገድ በመከተል ፊደል የላቸውም ላሏቸው ድምፆች ፊደል በመቅረጽ ልክ እንደ ትግርኛው መገልገል ይችሉ የነበረበት ዕድል ነበር፡፡ የአናባቢ ድምፆች በቂ አይደሉም ላሉትም አንዲት ምልክትን በመጠቀም ያሉትን አናባቢዎች በእጥፍ ማሳደግና ከበቂ በላይ በማድረስ ገጠመን ያሉትን ችግር በቀላሉና በአስተማማኝ ሁኔታ ሌሎችንም የድምፅ ሰጭ ምልክቶችን (ፎኒሞችን) ችግር በዚሁ መልኩ መቅረፍ ይቻል የነበረበት ዕድል ነበር፡፡ የሆነ ሆኖ ችግሩ ይህ ከሆነ እነዚህ ከአማርኛው የፊደል ገበታ ውጪ የሆኑ ፊደል ያልተቀረጸላቸው ድምፆች ካሉ ፊደላቱ ቢፈጠሩላቸው ፊደል የለውም ያሉትን ድምፅ በመሠየም ከሞራል ጥያቄና ከኢትዮጵያዊነት ወይም ከማንነት አንፃር ሳይቸግር ጤፍ ብድር እንዳይሆን የባዕድ ፊደላትን ከመጠቀም ተመልሰው በራሳቸውና ማንነታቸው በታተመበት ፊደላት እንዲጠቀሙ ያስችላቸዋል የሚለው አንደኛው ሲሆን፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ቋንቋችን ፎነቲክ መሆኑ እና ፊደሎቻችን ሲላበሪ መሆናቸው በወረቀት ቀለም ፍጆታና ተመሳሳይ ነገሮች አንፃር ከሌሎች ቋንቋዎች ፍጆታ በግማሽ እንዲቀንስልንና በጣም እንድንቆጥብ አስችሎናል፡፡ በዚህም ባሕሪው ፊደሎቻችን በመላው ዓለም የተለየና ተደናቂ እንዲሆኑ አስችሏቸዋል፡፡

ወደፊት ዓለም በሁለት ምክንያቶች የእኛችን ፊደሎች ለመጠቀም ይነሣሣል ወይም ይገደዳል የሚል እምነት አለኝ፡፡ አንደኛው ምክንያት አሁን እየተገለገሉበት ካሉት ፊደሎች ካሉባቸው ችግሮች ወይም አስቸጋሪነት አኳያ ቀላሉንና ምቹውን መንገድ ከመምረጥ አንፃር ሲሆን ሌላኛው ምክንያት ደግሞ ወደፊት ዓለም የሪሶርስ ወይም የጥሬ ዕቃዎች አቅርቦት ችግር በጣም አሳሳቢ ደረጃ እንደሚደርስ እሙን ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ገና ከወዲሁም ጀምሯል፡፡ ይህ መሆኑ ወጪንና ፍጆታን ለመቀነስ ወይም ለመቆጠብ ሲሉ ወጪና ፍጆታ ቆጣቢና በአጭር እና ጥቂት ቃላት ማለት የተፈለገን ነገር ያለአሻሚና አምታች ቃል መግለጽ የሚቻልባቸውን ፊደላት ወደ መምረጥ ሊያመጣቸው ወይም ሊያስገድዳቸው የሚያስችል ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ያኔ የእኛን ፊደላት ለመጠቀም ሲፈልጉ ምንአልባት አንዳንድ ድምፆቻቸው በእኛ የፊደል ገበታ ያልተገኙ እንደሆነ ሠይመው እንዲጠቀሙ ለማስቻል ነው የሚለው ደግሞ

ሌላኛው ምክንያቴ ነው። ቋንቋችን ወይም ፊደሎቻችን አሁን ባለበት አቋሙ እንኳን የብዙ ሀገሮችን ቋንቋዎች ያለምንም ችግር የማገልገል ሙሉ አቅም እና ብቃት እንዳለው ይታወቃል። እኔ ፩፻፹፪ ፊደላትን የቀረጽኩት ወይም የፈጠርኩት ፊደሎቻችን ሌሎች ቋንቋዎችን ለማገልገል ያንን ያህል ጉድለት ይኖራቸዋል በሚል ሳይሆን ፊደሎቻችን የት ድረስ የመስፋትና የመለጠጥ አቅምና ሀብት እንዳላቸው ለማሳየት ነው። እናም በእነዚህ ሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች አዳዲስ ፊደላትን ለመቅረጽ ወይም ለመፈልሰፍ በቃሁ።

የአቀራረጹ ወይም ያፈለሳሰፉ ሁኔታ የሚከተለውን ይመስስላል። የተፈጠሩት ፊደሎች ፩፻፹ወ፪ መሆናቸው ከላይ ተገልጿል። ፊደሎቹ የተቀረጹበት መንገድ በ፬ ይከፈላል፦

፩. ፍጹም አዳዲስ የሆኑ

፪. ልክ በዛጉዌ ሥርወ መንግሥት ጊዜ ፯ቱ ፊደላት የተፈጠሩበትን መንገድ በመጠቀም ለምሳሌ በሰ አናት ላይ ጭረት በማድረግ ሸ፣ ከነ ላይ ኘ፣ከተ ቸ፣ከከ ኸ፣ከዘ ዠ፣ከደ ጀ፣ከጠ ጨን ማግኘት እንደተቻለ ሁሉ። እንዲሁም ከዚያ በፊት ከዋናዎቹ ፊደላት አንዳንዶቹ በተፈጠሩበት መንገድ ለምሳሌ ሃሌታዋን ሀን በመገልበጥ በን ማግኘት እንደተቻለ፣ በበ አናት ላይ ቅጽል በማድረግ እሳቱ ሰን ማግኘት እንደተቻለ፣ ሠን በመገልበጥ ጠን ማግኘት እንደተቻለ ማለት ነው። እናም ነባሮቹ ፊደላት ባሉበት ሁኔታ ሆነው እንደአመቺነቱ ውበትን ሊጨምርላቸው በሚያስችል መልኩ እዝልና ቅጽል በማድረግ።

፫. አዲስ መንገድ በመፍጠር ነባሮቹን ፊደላት በማጋባትና እንዲወልዱ በማድረግ ማለትም ባልና ሚስት ልጆችን ሲወልዱ ልጅየው ወይም ልጅቷ ከእናቷ የሆነ ነገርን ከአባቷም የሆነ ነገርን በመውሰድ የራሷን ተፈጥሮ እንደምትይዝ ወይም እንደሚይዝ ሁሉ ፊደሎቹም ይህ ሁኔታ ሊታይባቸው ችሏል።

፬. ከነበራቸው አካል በማቅለል ወይም በመቀነስ ናቸው።

የአናባቢ የድምፅ ምልክቶቻቸውን በተመለከተ ግን የግድ የነባሮቹን እዝል እና ቅጽል መጠቀም ስለነበረብኝ ይህን ባላደርግና ሌላ ዓይነት የድምፅ ምልክቶችን ብጠቀም ግን

ሀ/መደናገርን እና የጥናት አቅምን የማባከን ችግሮች ስለሚፈጥር

ለ/ ፊደሎቹ የነባሮቹ ፊደሎች ቤተሰቦች መሆናቸው ይቀርና የሌላን ቋንቋ ፊደሎችን እንደመቀላቀል ዓይነት ባዕድና የማይግባቡ የመሆን ችግር ስለሚገጥማቸው እነኚህ ችግሮች እንዳያጋጥሙ ሲባል የሁሉም ፊደሎች የጋራ እሴት የሆኑትን የድምፅ ሰጪ ምልክቶችን እነዚህኞቹም ማለትም አዳዲሶቹ እንዲጋሩት አድርጌያለሁ።

ፈ ፉ ፊ ፋ ፌ ፍ ፎ
ነ ኑ ኒ ና ኔ ን ኖ
በ ቡ ቢ ባ ቤ ብ ቦ
የ ዩ ዪ ያ ዬ ይ ዮ
ጸ ጹ ጺ ጻ ጼ ጽ ጾ
ሰ ሱ ሲ ሳ ሴ ስ ሶ
ጰ ጱ ጲ ጳ ጴ ጵ ጶ

ወ ዉ ዊ ዋ ዌ ው ዎ
ጠ ጡ ጢ ጣ ጤ ጥ ጦ
ገ ጉ ጊ ጋ ጌ ግ ጎ
ተ ቱ ቲ ታ ቴ ት ቶ
ከ ኩ ኪ ካ ኬ ክ ኮ
ሐ ሑ ሒ ሓ ሔ ሕ ሖ
ረ ሩ ሪ ራ ሬ ር ሮ
ደ ዱ ዲ ዳ ዴ ድ ዶ

በ ቡ ቢ ባ ቤ ብ ቦ
ዐ ዑ ዒ ዓ ዔ ዕ ዖ
ሠ ሡ ሢ ሣ ሤ ሥ ሦ
[illegible]
ፀ ፁ ፂ ፃ ፄ ፅ ፆ
ሀ ሁ ሂ ሃ ሄ ህ ሆ

ሀ ሁ ሂ ሃ ሄ ህ ሆ
የ ዩ ዪ ያ ዬ ይ ዮ
ጸ ጹ ጺ ጻ ጼ ጽ ጾ
ቀ ቁ ቂ ቃ ቄ ቅ ቆ

**4ኛ. ቋንቋችን ለእያንዳንዱ ድምፅ የየራሱን ፊደል የቀረጸ (ፎነቲክ) እንደመሆኑ መጠን ለእያንዳንዱ ድምፅ ፊደል የመቅረጽ ግዴታ አለበትና ድምፆቹ እያሉ ፊደል ግን ለሌሏቸው ለጊዜው ለአምስት ድምፆች በነባሩ ፊደሎች ላይ ቅጽል በማድረግ የተቀረጹ ፊደሎችን፡፡**


፩. ለአንድ ነገር ኀዘኔታ ሲሰማን ማዘናችንን ለመግለጽ ከንፈር በመምረጥ የምናሰማው ድምፅ በሽሙጥ *"የሀበሻ የመጀመሪያ እርዳታ"* በማለት የምናውቀው ድምፅ ሲሆን ከ ም ፊደል እግር ላይ ጭረት አግድም በማስመር የራሱን ድምፅ እንዲይዝ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡

፪. ቁጭትና ብስጭት ሲሰማን፣ በአንድ ጉዳይ ላይ ያለመስማማትን ድንገት በቅጽበት የምንገልጽበትን ምላስን በላይኛው ድድ ላይ ወደ ውስጥ በመሳግ የምናሰማው ድምፅ ሲሆን እሱንም በ ጥ ፊደል እግር ላይ አሁንም የሠረዝ ምልክት በመጨመር ድምፁ የራሱ ፊደል እንዲኖረው ተሞክሯል፡፡

፫. አንድ ሰው በሚያወራበት ጊዜ እኛንም ከልብ የምንስማማበትን ነገር ሲናገር ድንገት ሳናውቀው በቅጽበት የምናሰማውን ድምፅ የሚወክል ሲሆን ከሐመሩ ሐ ራብዑ ወይም ሕ አናት ላይ ሠረዝ በማድረግ ድምፁ የራሱ ፊደል እንዲኖረው ለማድረግ ታስቧል፡፡

፬. ቃሉን በየዕለት ተዕለት ንግግራችን የምንጠቀመው ፊደል ግን የሌለው ምድቡ ከፍንጽቅ ፊደላት ውስጥ የሆነ ድምፅ አለ፡፡ ለምሳሌ እ---ቸው በጐንደር አማርኛ ጠብቆ ሲነበብ እ---ቸው /ተመልከቷቸዉ/ በሸዋ ላልቶ በሚነበበው ቃል ውስጥ አለ፡፡ በመሆኑም የ እግር ላይ እንደ ሁሉም ፍንጽቅ ፊደላት ሁሉ ሠረዝ በማድረግ ፍጹም የራሱን ፊደል እንዲይዝ ተደርጓል፡፡

፭. ምድቡ ከፍንጽቅ ፊደላት ውስጥ ሲሆን ፊደል ግን የለውም፡፡ በጐጃም ተወላጆች ንግግር ላይ የቁጣና የመደነቅ ድምፅ ሲያሰሙ የሚያወጡትን ድምፅ የሚይዝ በ ዋ እግር ላይ እንደሌሎቹ ፍንጽቅ ፊደላት ሁሉ የሠረዝ ምልክት በማድረግ ድምፁ የራሱ ፊደል እንዲኖረው ታስቧል፡፡



**5ኛ** ከረጅም ጊዜ ጀምሮ በፊደሎቻችን ላይ ለሚነሡ ጥያቄዎችና ቅሬታዎች ሁሉ ይህንን ጉዳይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሊዘጋ የሚችል የተጠናቀረ መልስ ጠለቅ ያለ ማብራሪያ ከማስረጃዎች ጋር (discourse Analysis) ቀረበ፡፡

እነኚህን ከላይ የተገለጹትንና ሌሎች በውስጣቸው ያሉትንም አዳዲስና ወጥ ወይም ንጥር(Original) ሥራዎች የያዘ የፈጠራና የምርምር ሥራ ነው፡፡


ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com